ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**




ለክቡር ጠቅላይ ሚንስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ፌድራል ዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ጠቅላይ ሚንስትር
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 1031
አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ
ነሓሴ 30 2006ዓም

ጉዳዩ ፤ ስለ ቀድሞዉ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ዓለም አቀፍ ማህበር መቋቋምና የሰብአዊ መብት ጥያቄ

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር

በቅድሚያ እኛ በመላዉ ዓለም በስደት የምንገኝ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አባላት በአንድነት ከምድር ጦር ፣ ከአየር ኃይል፣ከባህር ኃይል ፣ከፖሊስ ፣ከሚሊሺያና ከብሔራዊ ሠራዊት ኢ.ኤ.አ በግንቦት 28 ቀን 2014 በቀድሞዉ ጦር ኃይሎች የሰብአዊ መብት መከበር ዙርያ ያጠነጠነ ስምንት ነጥብ ያላቸዉ ዓላማ ይዘን በመነሳት (ዓለም አቀፍ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ማህበር) በሚል መጠሪያ ማህበር ማቋቋማችንን በዚህ አጋጣሚ እንገልፃለን። (በአሜሪካ ሀገር ያለችርፍ አገልግሎትና በሰብአዊ መብት ዙርያ ለመስራት እንድያስችለን በሕጋዊነት በይፋ የተቋቋምንበትን ህጋዊነት የሚያረጋግጥ ማስረጃም ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን ልከናል።

ክቡርነትዎ እንደሚያዉቁት በማንኛዉም ሀገር የአንድ ሀገር የመከላከያ ሠራዊት ከህዝቡ የወጣና የህዝብ አካል ሲሆን ፤ ዓላማዉ ደግሞ የሃገሩን ዳር ድንበር በወቅቱ ወይንም በጊዜዉ በስልጣን ላይ ባሉት መሪዎች ወይም መንግስት በሚሰጠዉ መመሪያ መሰረት በላቡ ,በደሙና በህይወቱ መስዋዕትነት ከፍሎ ዳር ድንበሩን ፤ የባህር በሩንና የአየር ክልሉን ማስከበር ነዉ።

እኛም የኢትዮጵያ የቀድሞዉ ጦር ኃይሎች አባላት በሃገራችን በኢትዮጵያ ቀደም ሲል በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት በኋላም በወታደራዊ መንግስት ዘመን ከህዝቡ አብራክ ወጥተን ሲወርድ ሲዋረድ ከቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን በወረስነዉ የጀግንነት ታሪክ ላይ ተመስርተን የዚህ የዛ መንግስት ሳንል ይህ የመከላከያ ሠራዊት በ1983 በኢህአዴግ በይፋ እስከፈራረሰበት ድረስ የሀገራችንን ዳር ድንበር ፣የአየር ክልላችንን ብሎም የባህር በሮቻችንን በመስዋዕትነት ስናስከብር እንደነበር ይታወቃል።

ሆኖም በ1983 ዓም የዚህን የቀድሞ ጦር ኃይሎች መፍረስ ተከትሎ ይህ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት ወታደራዊ መንግስት የመሰረተዉ ይመስል የደርግ ሠራዊት ወይም የደርግ ወታደር ፣ ኢሠፓ ወዘተ ,,,,, በሚል ያለምንም ጡረታ ወይንም ካሳ እንዲበተን ተደርጎ ይህ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ከነቤተሰቡ ሥራ አጥ ሆኖ በረሃብ ፣በችግርና በመከራ ያለኃጥያቱ እንዲቀጣ፣ እንዲሰቃይ፣ እንዲሞትና እንዲሰደድ ሆኖአል።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር

እንኳንስ ዲሞክራሲ አሰፍናለሁ ወይንም አስፋፋለሁ ፣ ለፍትህ ቆሜያለሁ ለሚል መንግስት ይቅርና ከዚህ በተቃራኒ በቆመ አምባገነን መንግስታት ስር እንኳን የሚገኝ የመከላከያ ሠራዊት አበላት የእከሌ ፣ የእከሌ ሠራዊት ተብለዉ የሚጠሩበት ወይም የሚበተኑበት አንድም ሀገር የለም። የመሪ እንጂ የሠራዊት መጥፎ የለም።

ይህንን የቀድሞ የአትዮጵያ ጦር ኃይሎች ኢህአዴግ በ1983 ዓም ያለ ስሙ ስም ሰጥቶ ከአፈረሰዉ ከአስር ዓመት በኋላ እንኳን በ1993 ዓም የኢህአዴግ መንግስት ከኤርትራ ጋር ጦርነት በገባበት ወቅት ፣ ይህ ኢህአዴግ የአፈረሰዉ፣የበተነውና አስሮ ያስቀመጠዉን ሠራዊት «እናት ሀገርህ ትፈልጋሃለች , ተነስ ተዋጋ » ተብሎ ሲጠየቅ ቂም ሳይዝ ከድሮዉም ዓላማዉ የሃገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ስለነበር ጥሪዉን ያለማመንታት ተቀብሎ በኢህአዴግ መንግስት አመራር ሰጪነት የሰሜን ሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ዘምቶ በአስር

• Phone 972 277 7741 • E-mail feafww@gmail.com • Web site address www.formerethiopianarmedforceworldwide.org

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**



ሺህዎች የሚቆጠሩ የህይወት መስዋዕትነት እንደከፈሉና እንደቆሰሉ ጦርነቱንም አቁሙ ባይባሉ ሻቢያን ጠራርጎ ከኤርትራ ምድር ሊያስወጡ እንደነበር የቅርብ ግዜ ትዝታ ነዉ።

ስለሆነም ይህ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለግለሰብ ወይንም ለድርጅት የቆመ ሳይሆን የሀገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር የቆመ ሠራዊት እንደነበር ከዚህ በላይ መረጃ ያስፈልጋል ብለን አናምንም። ዛሬም ቢሆን ከኢትዮጲያ ህዝብ ተመሳሳይ ጥያቄ ቢቀርብ ይህ ሠራዊት ተመሳሳይ መልስ ከመስጠት ወደኋላ የሚል እንዳልሆነ በዚህ አጋጣሚ ልናረጋግጥ እንወዳለን።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር

ይህ ሠራዊት በ1983 በህገወጥና ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ መፍረስ ብቻ ሳይሆን ከፈረሰም በኋላ ለብዙ አመታት ለሃገሩ ላደረገዉ አገልግሎትና መስዋዕትነት ጡረታና ካሳ ሲገባዉ ያለ ጡረታና ያለካሳ በመባረሩ በሠራዊቱም ሆነ በቤተሰቦቹ ላይ የደረሰዉ መከራና ስቃይ በዓለም ላይ በየትኛዉም ሀገር ያልተፈፀመና ህገወጥ ስለሆነ ክቡርነትዎ ይህንን ጉዳይ በጥልቀት በመርመር፤

1ኛ, ቢቻል ከቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አባላት ዉስጥ ፈቃደኛ የሆኑትንና ዕድሜያቸዉና የጤናቸዉ ሁኔታ የፈቀደላቸዉን አባላት የሃያ ሦስት አመታት ደሞዛቸዉን ፣ የማዕረግ ዕድገት ሂደታቸዉን ጠብቆ ወደ ሠራዊቱ እንዲመለሱ ይሆን ዘንድ

2ኛ, ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ የጡረታ መብታቸዉ እንዲጠበቅና የሃያ ሦስት ዓመታት ካሳም እንዲከፈላቸዉ፤

3ኛ, ከህግ ወንጀለኝነት ዉጪ በቀድሞዉ ጦር ኃይሎች አባልነታቸዉ እና ለሀገራቸዉ በሰሩት የጀግንነት ሥራ ብቻ እንደወንጀለኛ ተቆጥሮባቸዉ በእስር የሚሰቃዩትን አባሎቻችን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣

4ኛ ,በኤርትራም በረሃ ያለ ሃጥያታቸዉ በሠራዊት አባልነታቸዉ እና በሠሩት ጀግንነት ብቻ ከምድር በታች ታስረዉ የሚሰቃዩትን የቀድሞ የጦር ኃይሎች አባላት ከእሥር ለማስለቀቅ መንግስትዎ ከኤርትራ መንግስት ጋር በመደራደር እንዲለቀቁ እንዲያደርጉ፤

5ኛ, በቀድሞዉ የጀግኖች አምባ የሃገራችንን ዳር ድንበር፣ የአየር ክልላችንን እንዲሁም የባህር በራችንን ለማስከበር ሲታገሉ የቆሰሉና አካላቸዉ የጎደለ የቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች አባላት ለሃገር ዳር ድንብር መከበር የታገለ ሠራዊት እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ የሚባረርበት ፣የሚታሰርበት የሚገደልበትና የሚሰደድበት እንዲሁም ፍፁም ኢሰባዓዊ በሆነ መንገድ እንደ ጠላት ተቆጥረዉ ከአምባዉ በግፍ እንዲባረሩ በመደረጉ ፤ ብዙዎች በዚህ የተነሳ መድረሻ በማጣት ያለምንም ዕርዳታ ሜዳ ላይ ተጥለዉ የሞቱ ሲሆን የቀሩት ደግሞ በረንዳ አዳሪ ሆነዉ በልመና ሥራ ላይ የተሰማሩ መሆኑን በግልፅ እየታየ ነዉ። እንዲህ ዓይነት ግፍ በዓለም ላይ የሚፈፀምባት ብቸኛ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ስለዚህ እነዚህ በህይወት ያሉ ጀግኖች ተመልሰዉ ወደ ጀግኖች አምባ ወይም ተመሳሳይ ማዕከል መግባት እንዲችሉ፤

6ኛ በአለቀና በመጨረሻ ዕድሜያቸዉ በረሃብና በችግር የሚሰቃዩ በጣም ጥቂት የሆኑ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ አርበኞች አባላትም በዚህች በቀረቻቸዉ ዕድሜ እንኳን ከረሃብና ከችግር ተላቀዉ በአንድ ማዕከል ተሰባስበዉ እንዲረዱ፤

7ኛ, በመጨረሻም በ1983 የኢህአዴግ አዲስ አበባን መግባት ተከትሎ በሰላም መሳሪያቸዉን አሰቀምጠዉ ዕጃቸዉን እንዲሰጡ በአለቆቻችን ታዘዉ በሰላም ዕጃቸዉን በሰጡት የቀድሞ ጦር ኃይሎች አባላት ላይ እጅግ አሰቃቂ የግድያና ግርፋት በፈፀሙ ግለሰቦችና አሁንም በስልጣን ላይ ባሉ ግለሰቦች ላይ (ልክ በቀይ ሽብር እንደተወነጀሉት ግለሰቦችና ባለስልጣኖች ተይዘዉ ለፍርድ እንደቀረቡት ሁሉ) በዚህ ሠራዊት ላይ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድና የጄኔቫ ኮንቬንሽን ዉል በመጣስ ወንጀል የፈፀሙት ግለሰቦች ተይዘዉ ለህግ እንዲቀርቡና የዚህ አረመኔያዊ ድርጊት ሰለባዎችና ቤተሰቦቻቸዉ ፍትህን ያገኙ ዘንድ እንጠይቃለን።

• Phone 972 277 7741 • E-mail feafww@gmail.com • Web site address www.formerethiopianarmedforceworldwide.org

ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913**




ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር

እነዚህን ሰባት ጥያቄዎች ክቡርነትዎና መንግስትዎ በጥሞናና በዓፅንኦ ተመልክቶና  ተገንዝቦ ይህንን የሰብአዊ መብት ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በታላቅ ትህትና በተለያዩ  የዓለም አቀፍ ክፍሎች በስደት በምንገኝ የቀድሞ ጦር ኃይሎች አበላትና በራሴ ስም እንጠይቃለን።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆችዋ ለዘላለም ተከብራ ትኖራለች!!

ሻምበል አሸብር ገብሬ

*ashebir gebre*

ዓለም አቀፍ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ማህበር ቦርድ ሊቀመንበር

ግልባጭ

- ለተባበሩት የአሜሪካ  ስቴት ፕሬዚዳንት ክቡር  ባራክ ኦባማ
- ለተባበሩት የአሜሪካ  ስቴት ም/ፕሬዚዳንት ክቡር  ጆ ባይድን
- ለተባበሩት የአሜሪካ ስቴት ድፓርትመንት ክቡር   ጆን ኬሪ
- ለተባበሩት መንግስታት   ዋና ፀሐፊ  ክቡር ባን ኪ ሙን
- ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ክቡርት  ዶር ንኮሳዛና ድላሚኒ ዙማ
- ለተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን
- ለአመነስቲ ኢንተርናሽናል
- ለአለም ቀይ መስቀል
- ለወ/ሮ የሐረርወርቅ ጋሻዉ , የዓለም አቀፍ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ማህበር የሰብአዊ መብትና የዉጪ ግኑኝነት አምባሳደር
- ለሂዉማን ራይት ዎች
- በመላ ዓለም ለሚገኙ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አባላት
- ለምድር ጦር መረዳጃ ማህበር ዋሽንግተን ዲሲ
- ለአየር ኃይል መረዳጃ ማህበር ዋሺንግተን ዲሲ

• Phone 972 277 7741 • E-mail feafww@gmail.com • Web site address www.formerethiopianarmedforceworldwide.org

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**

**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

- ለባህር ኃይል መረዳጃ ማህበር ዳላስ ቴክሳስ

• Phone 972 277 7741 • E-mail feafww@gmail.com • Web site address www.formerethiopianarmedforceworldwide.org